# የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

## ከማዕድን ማምረት እና ምርመራ ሥራዎች የሚገኘው የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ የሚውልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 270/2013

መጋቢት 27 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ከማዕድን ምርመራ እና ማምረት ሥራ ባለፈቃድ የሚሰበሰበው የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ የሚውልበትን አግባብ እንዲሁም በፈቃድ ክልሉ የሚኖረው ማኅበረሰብ ተጠቃሚ መሆን እንዳለበት መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የማዕድን ምርመራ እና ማምረት ሥራ ባለፈቃዶች የማኅበረሰብ ልማት ላይ በመሳተፍ የማኅበራዊ ግዴታቸውን በአግባብቡ መወጣት እንዲችሉ ግልጽና ተገማች ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የማዕድንና የነዳጅ ሚኒስቴር በማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (በአዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው) አንቀጽ 82 (2) እንዲሁም በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 አንቀጽ 41 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "ከማዕድን ማምረት እና ምርመራ ሥራዎች የሚገኘው የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ የሚውልበትን አግባብ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 270/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

   1. "አዋጅ" ማለት የማዕድን ሥራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (በአዋጅ ቁጥር 816/2006 እንደተሻሻለው) ነው፤
   2. "ደንብ" ማለት የማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 423/2010 ነው፤
   3. በአዋጁ እንዲሁም በደንቡ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች ለዚህም መመሪያ ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
   4. "የፈቃድ ክልል አካባቢ ማኅበረሰብ" ማለት የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የሚደርስበት ማኅበረሰብ ነው፤
   5. "የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ" ማለት የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ፈቃድ ባለቤት ፈቃዱ በሚገኝበት አካባቢ በማኅበረሰብ ልማት ዕቅድ ውስጥ ለመሳተፍ የሚመደብ ገንዘብ ነው፤
   6. "ወረዳ" ወይም "የከተማ አስተዳደር" ማለት የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ፈቃድ የተሰጠበት ቦታ ወይም መሬት የሚገኝበት ወረዳ/ወረዳዎች/ ወይም የከተማ አስተዳደር ነው፤

7. "ባለፈቃድ" ማለት የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ሥራ ፈቃድ ከሚኒስቴሩ ወይም ከክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የወሰደ ሰው ነው::

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በማዕድን ምርመራ ሥራ እና በማዕድን ማምረት ሥራዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል::

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ከማዕድን ማምረት ሥራ ፈቃድ የሚገኝ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ መዋል፣ አስተዳደር እና ተጠቃሚነት</u>

4. <u>ስለ ማኅበረሰብ ልማት ፈንድ አከፋፈል ሁኔታ</u>

   1. ማንኛውም የማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በአዋጁ አንቀጽ 62 እና በደንቡ አንቀጽ 41 ድንጋጌ መሠረት ለማኅበረሰብ ልማት ተሳትፎ የሚከፍለውን ፈንድ በክልል የተሰጠ ፈቃድ ከሆነ ፈቃዱን የሰጠው የክልል ቢሮ/ኤጀንሲ/ጽሕፈት ቤት ለዚህ ዓላማ ብቻ በሚከፍተው የባንክ ሒሳብ እንዲሁም ፈቃዱን የሰጠው ሚኒስቴሩ ከሆነ ሚኒስቴሩ ለዚህ ዓላማ ብቻ በሚከፍተው_የባንክ ሒሳብ ገቢ ማድረግና ፈቃድ ለሰጠው አካል ገንዘቡን ገቢ ያደረገበት ማስረጃ ማቅረብ አለበት::

   2. በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ጊዜ ሲሆን ስምምነቱ ከተፈረመ ጊዜ አንስቶ በአሥራ ሁለት (12) ወራት ውስጥ አምሣ በመቶውን (50%) በአንድ ጊዜ ይከፍላል፤ ቀሪውን አምሣ በመቶ (50%) ደግሞ የመጨረሻው የዝግጅት ዓመት መጀመሪያው ወር ላይ በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት::

   3. በማዕድን ማምረት ወቅት ሲሆን በየዓመቱ የምርት ዓመቱ ባለቀ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት::

   4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም በማዕድን ማምረት ቅድመ ዝግጅት ወቅት ባለፈቃዱ ሁሉንም ክፍያ በአንድ ጊዜ መክፈል ከፈለገ በመጀመሪያ የዝግጅት ዓመት ውስጥ መክፈል ይችላል::

5. <u>የፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት</u>

   1. ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል:-

      ሀ/ የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ባለፈቃድ በስምምነት ወይም በደንቡ የተደነገገውን የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ለዚሁ ተግባር በተከፈተው የባንክ ሒሳብ ጊዜውን ጠብቆ ማስገባቱን መከታተል፤ መግባት በሚገባው ጊዜ ያላስገቡ ባለፈቃዶችን ለይቶ የፈንድ

ለ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ገንዘብ ወደ ባንክ ሒሳብ በገባ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተጠቃሚው ማኅበረሰብ ለሚገኝበት እንደ ሁኔታው ለክልል፣ ዞን ወይም ወረዳ የገንዘቡን መጠን፣ ያስገባው ባለፈቃድ ማንነት፣ ከየትኛው ፈቃድ እና የማዕድን ዓይነት ገቢ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማሳወቅ፤

ሐ/ የክልሉ የማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት ከወረዳው የቀረበውን የፕሮጀክት ዕቅድ አጽድቶ ለሚኒስቴሩ ሲያቀርብ የታቀደው ሥራ መጀመር እንዲችል የፈንዱን አምሣ በመቶ (50%) ዕቅዱ ጸድቶ በቀረበ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ለክልሉ ማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት እንዲደርሰው ማድረግ፤ የክልሉ የማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት ሥራው ግማሽ ያህል መሠራቱን አረጋግጦ ለሚኒስቴሩ ሲገልጽ ቀሪውን የፈንዱን አምሣ በመቶ (50%) በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ለክልሉ ማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት እንዲደርሰው ማድረግ፤

መ/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሐ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የታቀደው ሥራ ግንባታ ላይ ያላተኮረና ለማኅበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የውስጥ ቁሳቁስና ተጨማሪ ዕቃዎች ማሟላት ሲሆን በጸደቀው ፕሮፖዛል መሠረት ለወረዳው የተመደበው የማኅበረሰብ የልማት ፈንድ በአንድ ጊዜ እንዲላክ ማድረግ፤

ሠ/ የማኅበረሰብ ልማት ፕሮጀክቱ በዕቅዱ መሠረት እየተሠራ መሆኑን የመሥክ ክትትል በማድረግ ግብረመልስ መስጠት፤

ረ/ የተሠራው የልማት ሥራ ሲጠናቀቅ እንደ ሁኔታው ከክልሉ፣ ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደር እና ፈንዱን ከሰጠው ባለፈቃድ ጋር በመሆን ለተሰራው ፕሮጀክት ማኅበረሰቡ እውቅና እንዲሰጠው በማድረግ የሚመለከተው ዘርፍ መሥሪያ ቤት እንዲረከበው ማድረግ::

ሰ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የሚጠቀመው ማኅበረሰብ በተለያዩ ክልሎች ወረዳዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማኅበረሰብን የሚያቅፍ ከሆነ እንደሁኔታው ሁለቱ ክልሎች ወይም ወረዳዎችን በማስተባበር ፈንዱን ሥራ ላይ እንዲውል ድጋፍ ማድረግ፤

2. የክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የማዕድን ምርመራ ወይም ማምረት ባለፈቃድ በስምምነት ወይም በደንቡ የተደነገገውን የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ለዚሁ ተግባር በተከፈተው የባንክ ሒሳብ ጊዜውን ጠብቆ ማስገባቱን መከታተል፤ መግባት በሚገባው ጊዜ ያላስገቡ ባለፈቃዶችን ለይቶ የፈንድ ገንዘቡን እንዲያስገቡ ማድረግ፤

ለ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ገንዘብ ወደ ባንክ ሒሳብ በገባ በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ተጠቃሚው ማኅበረሰብ ለሚገኝበት እንደ ሁኔታው ዞን፣ ወረዳ ወይም ቀበሌ

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

6. <u>የወረዳ አስተዳደር ወይም የከተማ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት</u>

የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነው ማኅበረሰብ የሚገኝበት ወረዳ/ወረዳዎች/ አስተዳደር ወይም ከተማ አስተዳደር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አለበት፡-

1. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ ለማዋል የሚችል የተለያዩ ማኅበረሰቡን ሊወክሉ የሚችሉ አባላት_ያሉበት ኮሚቴ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት ማቋቋም፤
2. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የሚጠቀመው ማኅበረሰብ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማኅበረሰብ የሚያቅፍ ከሆነ ሁለቱ ወረዳዎች ተወያይተው ፈንዱን ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤
3. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ መጠን ለአንድ ለሚታይ የማኅበረሰብ ልማት ሥራ መዋል የሚችል መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ለክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ማቅረብ፤ የማኅበረሰብ ልማት ፈንዱ በቂ ከሆነ ለምን ሥራ መዋል እንደሚችል በመለየት የግዥ ሕጉን ተከትሎ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፤
4. የማኅበረሰብ ልማት ፈንዱ ለአንድ ሥራ በቂ አለመሆኑን ካረጋገጠ ይህንኑ ለክልሉ፣ ገንዘቡን ላስቀመጠው አካል እንዲሁም ፈንዱን ለሰጠው ባለፈቃድ በጽሑፍ መግለጽ፤
5. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ ለማዋል የወረዳው አስተዳደር የማኅበረሰቡን ፍላጎት ያማከለ ፕሮጀክት ዕቅድ ወይም ፕሮፖዛል ፈንዱ መኖሩን ባወቀ በ ሰላሳ (30) ቀናት ወስጥ ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፤ የጸደቀውን የፕሮጅክት ፕሮፖዛል በአሥራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ ለክልሉ የማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት ማቅረብ፤
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሚዘጋጀው ፕሮጅክት ዕቅድ ወይም ፕሮፖዛል የወረዳው አስተዳደር የሚያቋቁመውን ኮሚቴ በማማከር እንዲሁም ተጠቃሚውን ማኅበረሰቡ ካለው የልማት ፍላጎት ለየትኛው ቅድሚያ መሰጠት እንዳለበት ማኅበረሰቡን ማወያየት፤
7. የማኅበረሰብ ልማት ሥራ አምሣ በመቶ (50%) ተሠርቶ ሲጠናቀቅ ለክልሉ ፈቃድ ሰጪ ሥራው መጠናቀቁ በማሳወቅ ቀሪው አምሣ በመቶ (50%) እንዲላክ መጠየቅ፤
8. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የሰጠው ባለፈቃድ ማንነት፣ የፈንዱን መጠን እና ከየትኛው ማዕድን ፈቃድ እና ዓይነት እንደተገኘ ለማኅበረሰብ ማሳወቅ፤
9. የሥራውን አፈጻጸም በየጊዜው ለማኅበረሰቡ፣ ፈንዱን ላስቀመጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን እና ፈንዱን ለሰጠው ባለፈቃድ በየሦስት (3) ወሩ ሪፖርት ማቅረብ፤
10. በጸደቀው ዕቅድ ወይም ፕሮፖዛል መሠረት ሥራ ላይ ለማዋል ፈንዱን ካስቀመጠው የክልል ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ጋር ውል መፈራረም እና በሚገባ መፈጸም፤
11. ለመሥራት የታቀደው የማኅበረሰብ ልማት ሥራ ሲጠናቀቅ ፈንዱን ላስቀመጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን እና ፈንዱን ለሰጠው ባለፈቃድ አጠቃላይ ሪፖርት ማቅረብ፤

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum
መዝገብ ቤት
RECORD

የገንዘቡን መጠን፣ ያስገባው ባለፈቃድ ማንነት፣ ከየትኛው ፈቃድ እና የማዕድን ዓይነት ገቢ እንደሆነ በመጥቀስ በጽሑፍ ማሳወቅ፤

ሐ/ ለማኅበረሰብ ልማት ሥራ ኮሚቴ መቋቋሙን ማረጋገጥ፤ በሚመለከተው የወረዳ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የሚቀርበውን ዕቅድ በቀረበለት በ 30 ቀናት ውስጥ ገምግሞና አጽድቆ የሥራ ዕቅዱ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ፣ ዕቅዱ ከሀገራችን አጠቃላይ የልማት ዕቅድ አንጻር መገምገም፤ ግብረመልስ መስጠት፣ ዕቅዱ በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን ማረጋገጥ፤

መ/ ለልማቱ የተመደበው ፈንድ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እና የልማት ሥራው ደረጃውን በጠበቀ አግባብ መከናወኑን ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደር እና ፈንዱን ከሰጠው ባለፈቃድ ጋር በመሆን ማረጋገጥ፤ የልማት ሥራውን በየጊዜው መከታተልና መደገፍ፤

ሠ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ሥራ ላይ መዋሉን የሚከታተል ኮሚቴ መቋቋሙን ማረጋገጥ፣ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

ረ/ ከወረዳ አስተዳደር ጋር ፈንዱን ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ውል መግባት እና ማስፈጸም፤

ሰ/ የተዘጋጀው ዕቅድ ገንዘቡን ላስቀመጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን በ ሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ እንዲደርስ ማድረግ፤

ሸ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ መጠን ለአንድ ለሚታይ የማኅበረሰብ ልማት ሥራ መዋል የሚችል መሆኑን እና አለመሆኑን በወረዳው የቀረበለትን ኃሳብ ማረጋገጥ፤ የማኅበረሰብ ልማት ፈንዱ ለጊዜው የሚታይ የማኅበረሰብ ልማት ለማከናወን በቂ አይደለም ብሎ ካመነ ዕቅድ ማዘጋጀት ሳያስፈልግ ሌላ ተመሳሳይ ፈንድ እስኪገኝ ድረስ ገንዘቡ እንዲቀመጥ መወሰን፤ ፈቃዱ የተሰጠው በሚኒስቴሩ ሲሆን ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ፤

ቀ/ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የሚጠቀመው ማኅበረሰብ በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ ነዋሪ የሆነ ማኅበረሰብን የሚያቅፍ ከሆነ ሁለቱን ወረዳዎች በማስተባበር ፈንዱን ሥራ ላይ እንዲውል ድጋፍ ማድረግ፤

በ/ የማኅበረሰብ ልማት ሥራ አምሣ በመቶ (50%) መሠራቱ በማረጋገጥና እና ወረዳው በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት ጥያቄው በቀረበ በአሥራ አምስት 15 ቀናት ውስጥ ቀሪውን አምሣ በመቶ (50%) መላክ፤

ተ/ የተሠራው የልማት ሥራ ሲጠናቀቅ ከወረዳ ወይም ከከተማ አስተዳደር እና ፈንዱን ከሰጠው ባለፈቃድ ጋር በመሆን ለተሰራው ፕሮጀክት ማኅበረሰቡ እውቅና እንዲሰጠው

12. የልማት ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ከኮሚቴው ጋር በመሆን በቀጣይ መደበኛ የሆነ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሚመለከተው የዘርፍ መሥሪያ ቤት እንዲረከበውና በበላይነት እንዲያስተዳድረው ማድረግ፤

13. በማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የተሰራውን ሥራ ፈንዱን ካስቀመጠው ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን፣ ፈንዱን ከሰጠው ባለፈቃድ፣ የተጠናቀቀውን የልማት ፕሮጀክት የተረከበው የዘርፍ መሥሪያ ቤት እና ማኅበረሰቡ ባለበት እውቅና እንዲሰጠው ማድረግ፡፡

7. <u>ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነው ማኅበረሰብ የሚገኝበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ይህ ፈንድ ሥራ ላይ መዋሉን የሚከታተል የሚከተሉትን አባላት ያያዘ ኮሚቴ ማቋቋም አለበት፤

1. ከማኅበረሰብ ልማት ፈንዱ ተጠቃሚ ማኅበረሰብ በሥነ-ምግባራቸው ምስጉን የሆኑ አራት (4) ሰዎች፣
2. የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳዳሪ ሁለት (2) ሰው፣ አስተዳዳሪው ሰብሳቢ
3. በወረዳው ወይም በከተማ አስተዳደር የማዕድን ዘርፍ ጽሕፈት ቤት ሁለት (2) ሰው ሆኖ አንዱ ጸሐፊ ይሆናል፣
4. ከወረዳው ወይም ከከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ጽሕፈት ቤት አንድ (1) ሰው፣
5. ከሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጽሕፈት ቤት አንድ (1) ሰው፣
6. የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ከሰጠው ባለፈቃድ አንድ (1) ሰው፤ ባለፈቃዶቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ ከየባለፈቃዱ አንድ (1) ሰው፣
7. እንዳስፈላጊነቱ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት፡፡

8. <u>የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡-

1. ለሚከናወነው የልማት ሥራ የማኅበረሰቡን ፍላጎት በማወያየት መለየት፤
2. ወረዳው ለሚቀርጸው የልማት ዕቅድ ምክረ ኃሳብ ማቅረብ፣ ሥራው በዕቅዱ መሠረት በሚገባ መተግበሩን መከታተል፤
3. በማኅበረሰብ ልማት ሥራው ላይ ግድፈት ወይም ቅሬታዎች ሲያጋጥሙ እንደ ሁኔታው ለክልል የማዕድን ዘርፍ መሥሪያ ቤት ወይም ለወረዳው አስተዳደር በጽሑፍ ማሳወቅ፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር

9. <u>የዘርፍ መሥሪያ ቤት ኃላፊነት</u>

በማኅበረሰብ ልማት ፈንድ የሚሠራው የማኅበረሰብ ልማት ሥራ በሚከናወንበት ወቅት እንዲሁም ከተጠናቀቀ በኋላ ፕሮጀክቱ የሚመለከተው የክልል ወይም የወረዳ የዘርፍ መሥሪያ ቤት፤

1. የልማት ሥራው ሲታቀድ እንደ ሀገር የተቀመጠውን የዘርፉን ተፈላጊ ደረጃ መሠረት በማድረግ መታቀድ እንዲችል አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፤
2. የልማት ሥራው በአግባቡ እንዲካሄድ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤
3. ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀም በኋላ ተረክቦ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደረጋል፣ አስፈላጊውን ክትትል፣ ጥበቃና እንክብካቤ ያደርጋል፡፡

10. <u>የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ ሲሆኑ የሚገባቸው የማኅበረሰብ ክፍል</u>

ከማዕድን ማምረት ሥራ ባለፈቃድ በሚገኘው ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆነው ማኅበረሰብ ፈቃዱ የሚገኝበት ወረዳ ወይም ወረዳዎች ሲሆን በማዕድን ማምረት ሥራ ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የሚደርስበት ማኅበረሰብን ያካትታል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>
## <u>ከማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ የሚገኝ የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ</u>

11. <u>የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ እንዲከፈል የማድረግ ኃላፊነት</u>

በአዋጁ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 3 እና በደንቡ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ መሠረት ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን እንደአግባቡ የማዕድን ምርመራ ሥራ ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ፈቃዱን ከመስጠቱ በፊት ከፈቃድ ጠያቂው ጋር በመደራደር በፈቃድ ክልሉና አካባቢው ለሚኖር ማኅበረሰብ ልማት ሥራ ዕቅድ ላይ እገዛ ሊያደርግ የሚችል ፈንድ እንዲመደብ ማድረግ አለበት፡፡

12. <u>የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ስለ መመደብ</u>

1. ማንኛውም የማዕድን ምርመራ ባለፈቃድ በደንቡ አንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በማዕድን ምርመራ ሥራ ፈቃድ ቦታ አካባቢ ላይ ለሚኖሩ ማኅበረሰብ የልማት ፕሮግራም ሊያግዝ የሚችል የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ከፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ጋር በሚደረግ ድርድር የሚወሰነውን ፈንድ መመደብ አለበት፡፡
2. በመጀመሪያው የምርመራ ዓመት ስምምነቱ ከተፈረመ ጊዜ አንስቶ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ በአንድ ጊዜ መክፈል ያለበት ሲሆን በቀሪው እያንዳንዱ የምርመራ ዓመት ዓመቱ ባለቀ በሰላሳ (30) ቀናት ውስጥ በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት፡፡

ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)

3. ማንኛውም ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን የማኅበረሰብ ልማት ፈንዱ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5፣ 6፣ 7፣ 8 እና 9 ድንጋጌዎች መሠረት ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

13. <u>የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው የማኅበረሰብ ክፍል</u>

ከማዕድን ምርመራ ሥራ ባለፈቃድ በሚገኘው ፈንድ ተጠቃሚ የሚሆነው ማኅበረሰብ ፈቃዱ የሚገኝበት ወረዳ ወይም ወረዳዎች ሲሆን በማዕድን ምርመራ ሥራ ምክንያት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የሚደርስበት ማኅበረሰብን ያካትታል።

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. <u>የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ በጥሬ ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ</u>

በዚህ መመሪያ መሠረት ለማኅበረሰብ ልማት የሚመደብ ማንኛውም ፈንድ/ገንዘብ ለማኅበረሰብ ልማት ሥራ ብቻ መዋል ያለበት ሲሆን በማንኛውም አግባብ በጥሬ ገንዘብ ሊከፋፈል አይችልም።

15. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

1. ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም የምርመራ ወይም የማምረት ሥራ ባለፈቃድ ይህ መመሪያ በሥራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ማድረግ የሚገባው ተሳትፎ በዚህ መመሪያ መሠረት መሆን አለበት።
2. ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ ባለሥልጣን ይህ መመሪያ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ለሚሰጣቸው ፈቃዶች የማኅበረሰብ ልማት ፈንድ ማስተዳደር ያለበት በዚህ መመሪያ መሠረት መሆን አለበት።

16. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መጋቢት 27 ቀን 2011 ዓ.ም**

**ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር)**
**የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር**
**ሚኒስትር**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum